በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

የ7ኛ ክፍል አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ የመጀመሪያ ሴሚስተር ማጠቃለያ ፈተና ማዘጋጃ ቢጋር

ህዳር/2017 ዓ.ም

መግቢያ

ሰነዱም የ፮ ክፍል አማርኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የማጠቃለያ ፈተና ቢጋር እና የጥያቄ አይነቶችን በዝርዝር ያሳያል። ይህ ሰነድ አራት ዋና ዋና **የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት** የማጠቃለያ ፈተና ቢጋርን የፈተና ይዘት ቢጋር፣ የክህሎት ደረጃ ቴስት ቢጋር እና የጥያቄ አይነቶች ቢጋር ናቸው።።የፈተና ይዘት ቢጋር ደግሞ ለፈተናው የተመረጡት ይዘቶችና ከእያንዳንዱ ይዘት የተውጣጣውን የጥያቄ ብዛት ይዟል። የክሕሎት ደረጃ ቴስት ቢጋር ዝቅተኛ የመማር ብቃትን መሰረት ያደረገ የክህሎት ክፍፍል ቀርቦበታል። እንዲሁም የጥያቄ አይነቶች ቢጋር እያንዳንዱ ይዘት በየትኛው የፈተና አይነት እንደሚካተት ቀርቦበታል።

ይህ ቴስት ቢጋር የተማሪዎችን ዝቅተኛ የመማር ብቃት፣ የትምህርት ዓላማ እና የትምህርት ክፍለ ጊዜ ብዛት መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። ስለሆነም እያንዳንዱን ይዘት በቢጋሩ ለማካተት ተሞክሯል። የጥያቄዎቹ ብዛት መሰረት የሚያደርገውም ለትምህርቱ የተሰጠውን የክፍለ ጊዜ ብዛት ነው። በዚህም መሰረት ለይዘቱ የተሰጠው የክፍለ ጊዜ ብዛት ሲባዛ ጠቅላላ የጥያቄ ብዛት ሲካፈል ጠቅላላ የክፍለ ጊዜ ብዛት በሚል ቀመር ተሰልቶ ተዘጋጅቷል። ስለሆነም መምህራን ይህንን የቴስት ቢጋር ተከትለው ፈተናዎችን ቢያዘጋጁ ወጥ አሰራር እንዲኖር ያደርጋል። ቢጋሩ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና የሚጠበቅ ዝቅተኛ የመማር ብቃት (minimum learning competency) መሰረት ያደረገ ነው። ይህንን ተከትሎም ፈተናው በሁለት መንፈቀ ዓመት ተከፍሎ ቀርቧል። ሁለቱ መንፈቀ ዓመታት እያንዳንዳቸው 40 ጥያቄዎችን የሚያካትቱ ሲሆን በድምሩ 80 ጥያቄዎችን አካትተዋል። ከጥያቄዎች አይነት አንጻር ደግሞ 5 ጥያቄዎች እውነት/ሐሰት፣ 5 ማዛመድ፣ 25 የምርጫ ጥያቄዎች፣ 3 የዳሽ ሙላ ጥያቄዎች እና 2 የሰርቶ ማሳየት ጥያቄዎች ናቸው። ከተማሪዎች ክሕሎት አንጻር ደግሞ አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች መካከለኛ ክብደት ያላቸው ሲሆኑ ቀላል እና ከባድ ጥያቄዎች ደግሞ የተመጣጠኑ ናቸው። በዚህም መሰረት መካከለኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ግንዛቤን፣ መረዳትንና ትግበራን የሚጠይቁ) 20 (50%)፣ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማስታወስን የሚጠይቁ) 12 (30%)፣ እንዲሁም ከፍተኛ ክብደት ያላቸው ጥያቄዎች (ማሰላሰልን፣ ማደራጀትን፣ መተንተንንና መገምገምን የሚጠይቁ) 8 (20%) ናቸው።

ክፍል፡- 7ኛ

የት/ት ዓይነት፡- አማርኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ

የተቀመጠለት ክፍለ ጊዜ ብዛት፡- 57

የትምህርት ዘመን፡- 2017ዓ.ም

ምዕራፍ	ይዘት	ክፍል ጊዜ	የትምህርት ባህርይ መለኪያዎች				አጠቃላይ የጥያቄ ብዛት በት/ት ባህርይ መለኪያዎች	በመቶኛ ሲገለፅ
			እውቀት /Knowledeg/	መረዳት፣ /Comprehension/	ትግበራ /Application/	ማደራጀት መተንተን፣ መገምገም		
ምዕራፍ አንድ	ተፈጥሮን ማድነቅ	18	5	3	1	3	13	12%
	መናገር 1.1 የንግግር መመሪያ			2(እ/ሀ)			2	
	ንባብ 1.2 ጥሩ የንባብ ልምድ		1(ዳሽ)				1	
	1.3 የተለመዱና ያልተለመዱ ቃላት ፍቺ		2(አ፣ም)				2	
	ጽሕፈት 1.4 አንቀፅ መፃፍ			1(ም)	1(ፃ)		2	
	ቃላት 1.5 ተዘውታሪ ቃላት		3(ም)	1(አ)			4	
	ሰዋስው 1.6 ዓረፍተ ነገር					2(ም)	2	
ምዕራፍ ሁለት	የቤተሰብ እቅድ	9	2	2	2		6	6%
	መናገር 2.1 ክርክር			1(ም)			1	
	ንባብ 2.2 የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ		1(አ)				1	
	ጽሕፈት 2.3 ኢ- መደበኛ ዕሁፍ			1(ም)	1(ዳሽ)		2	
	ቃላት 2.4 አውዳዊ ፍች			1(ም)			1	
	ሰዋስው 2.5 የአሁን ጊዜ አመልካች		1(ም)				1	

ምዕራፍ ሶስት	በጎ ፈቃደኝነት	9	2	4			6	6%
	ማዳመጥ 3.1 የማዳመጥ መመሪያ		1 (እ/ሀ)	1(ም)			2	
	ጽሕፈት 3.2 የማግባቢያ ፅሁፍ			1 (ም)			1	
	ቃላት 3.3 ድርብ ቃላት		1(ም)				1	
	ሰዋስው 3.4 ነጠላና ብዙ ቁጥር			1(ፃ)1 (እ/ሀ)			2	
ምዕራፍ አራት	የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ	12	1	8			9	9%
	ማዳመጥ 4.1 የቃላት አውዳዊ ፍች			2(ም)			2	
	መናገር 4.2 የህይወት ታሪክ መመሪያ			1(ም)			1	
	ንባብ 4.3 የቃላት ተቃራኒ ፍቺ			1(አ)			1	
	4.4 ፊሊጣዊና ምሳሌያዊ አነጋገር			1(ም)			1	
	ጽሕፈት 4.5 አያያዝ ቃላትና ሀረጋት			1(ም)			1	
	ቃላት 4.6 ተዘውታሪና ፊሊጣዊ ቃላት		1 (ም)				1	
	ሰዋስው 4.7 ስማዊ ሀረግ			2(ም)			2	
ምዕራፍ አምስት	ውሃና ጥቅሙ	9		5	1		6	6%
	ማዳመጥ 5.1 ዐ.ነገር ማሟላት			1(ዳሽ)			1	
	ጽሕፈት 5.2 ተራኪ ፅሁፍ			1 (ም)			1	
	ቃላት 5.3 የቃላት እማሬያዊና ፍካሬ ፍቺ			2(አ፣እ/ሀ)	1(ም)		3	
	ሰዋስው 5.4 ገቢርና ተገቢሮ ዐ.ነገር			1(ም)			1	

መግለጫ፤- እ/ሀ ፡ እውነት /ሀሰት = 5፤ አ፡ አዛምድ = 5 ፤ ም፡ ምርጫ = 25 ፤ ዳ፡ ዳሽ ሙላ = 3፤ ፃ፡ፃፍ (ሰርቶ ማሳየት) = 2 ማለት ነው።